# መጽሐፈ ሩት ላይ የተጠየቁ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው




## አዘጋጅ፡- በትረ ማርያም አበባው

**(የመጻሕፍት ብሉያት፣ የመጻሕፍት መነኮሳትና የመጻሕፍት ሊቃውንት ትርጓሜ መምህር)**


**ህዳር ፱፣ ፳፻፲፮ ዓ.ም**

## መጽሐፈ ሩት ላይ የተጠየቁ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

፩. "ወደዚህ ቅረቢ ምሳም ብዪ፥ እንጀራሽንም በሆምጣጤው አጥቅሺ" ይላል (ሩት 2፥14)። በሆምጣጤው ጥቀሽ ሲል ትርጓሜው ምንድን ነው?

መልስ፦ ሆምጣጤ የሚባለው መራራነት ያለው የከረመ ወይን ወይም የሚያሰክር መጠጥ ነው። በዚህ እያጣቀስሽ ብዪ ማለት ነው።

፪. "ዋርሳ መሆኔ እውነት ነው፤ ነገር ግን ከኔ የሚቀርብ ዋርሳ አለ" ይላል (ሩት 3፥12)። ከእኔ የሚቀርብ ዋርሳ አለ ሲል ትርጓሜው ምንድን ነው?

መልስ፦ ዋርሳ በእስራኤል ባህል መሠረት አንድ ሰው ሚስት አግብቶ ልጅ ሳይወልድ ቢሞት የሟቹ ወንድሙ ወይንም የቅርብ ዘመዱ የሟቹን ሚስት አግብቶ በሕግ ለሟቹ ዘር የሚተካበት መንገድ ነው።

፫. ሩት ፩፥፲፭ "ኑኃሚንም እነሆ ባልንጀራሽ ወደ ሕዝቧና ወደ አማልክቷ ተመለሰች አንችም ደግሞ ከባልንጀራሽ ጋራ ተመለሽ አለቻት" ይላል። ሩትና ዖርፋ ቀድሞ በእግዚአብሔር አያምኑም ነበር ማለት ነው? ዝቅ ብሎም ሩት ለኑኃሚን አምላክሽ አምላኬ ይሆናል ብላለች እንዲህስ ከሆነ ለምን ከማያምኑ ጋ ተጋቡ በመጀመርያ።

መልስ፦ የአቤሜሌክ ልጆች ሩትንና ዖርፋን ሲያገቡ ወደአይሁዳዊ እምነት ቀይረዋቸው ይሁን አይሁን የተገለጸ ነገር አላገኘሁም። ባሎቻቸው ሲሞቱ ዖርፋ ከወገኖቿ ጋር ወደጣዖት አምልኮዋ እንደተመለሰች ተገልጿል። ሩት ግን አምላክሽ አምላኬ ይሆናል ብላ ኑኃሚንን ተከትላታለች። መጀመሪያውንም ሳያምኑ አግብተዋቸው ከሆነ ሕገ ኦሪትን ሽረው አግብተዋቸው ነበረ ማለት ነው። አሳምነው አግብተዋቸው ከሆነም መልካም አድርገው ነበረ ማለት ነው። ነገር ግን በዚህ ዙሪያ እንዴት እንደነበረ ተጨማሪ የተጻፈ ስላላገኘሁ አላውቀውም።

፬. ሁሉን የሚችል አምላክ አስመርሮኛልና መራራ በሉኝ እንጅ ኑኃሚን አትበሉኝ ስትል። እግዚአብሔር ሰዎችን ያስመርራል?

መልስ፦ እግዚአብሔር ሰውን አያስመርርም። ነገር ግን ረድኤቱን ባይሰጥ ስለሆነ ይህ ሁሉ የደረሰባት ረድኤት መንሣቱን ከማስመረር ቆጥራ ኑኃሚን እንዲህ አለች። መራራ ሕይወትን ስለኖረች የራሷን መመረር ለመግለጽ የተናገረችው ነው።

፭. "ኑኃሚንም ምራቶቿን ኺዱ ወደእናቶቻችኹም ቤት ተመለሱ በእኔና በሞቱት እንዳደረጋችኹ እግዚአብሔር ቸርነት ያድርግላችኹ" ይላል። ምንድን ነበር በእርሷ እና በሞቱት ያደረጉት?

መልስ፦ ያርፋና ሩት ኑኃሚን ቀሪ ልጆች እንደሌሏት እያወቁ ተከትለንሽ እንሄዳለን ማለታቸው ይህ ትልቅ የቸርነት ሥራ ነው። እናታቸውን መንከባከብ ለሞቱት ልጆቿም እንደማሰብ ስለተቆጠረላቸው ነው እንዲህ መባሉ።

፮. "እነርሱም ተቀመጡ። ቦዔዝም የቅርብ ዘመዱን ከሞዐብ ምድር የተመለሰችው ኑኃሚን የወንድማችንን የአቢሜሌክን ጢንጦ ትሸጣለች" ይላል (ሩት 4፥3)። ጢንጦ ምንድን ነው?

መልስ፦ ጢንጦ የሚባለው የመሬት ርስት ድርሻ ነው።

፯. "ቦዔዝም፦ እርሻውን ከኑኃሚን እጅ በምትገዛበት ቀን፥ ለሞተው በርስቱ ስሙን እንድታስነሣለት ከሚቱ ሚስት ከሞዓባዊቱ ከሩት ደግሞ ትገዛለህ አለ" ይላል (ሩት 4፥5)። ለሞተ ሰው በርስቱ ስሙን እንድታስነሣለት የሚለው ምን ለማለት ነው?

መልስ፦ በዋርሳ ሕግ የቅርብ ዘመድ የሚቱን ሚስት ካገባ በኋላ የሚወለደው ልጅ በሕግ በሞተው ሰው ይጠራል። ልጁን የወለደው ሌላ ሰው ቢሆንም ነገር ግን ወልዶ ስሙ እንዲነሣለት (እንዲታወስለት) አደረገ ማለት ነው።

፰. "መቤዠት ብትወድድ ተቤዠው፤ መቤዠት ባትወድድ ግን ከአንተ በቀር ሌላ ወራሽ የለምና፥ እኔም ከአንተ በኋላ ነኝና እንዳውቀው ንገረኝ አለው። እርሱም። እቤዠዋለሁ አለው" ይላል (ሩት 4፥4)። በዚህ ዐውድ "መቤዠት" ሲል ምን ለማለት ነው?

መልስ፦ መቤዠት ማለት በዚህ አግባብ ሚስቱን አግብተህ ስለእርሱ ለእርሱ በእርሱ ስም የሚጠራ ልጅ ውለድለት ማለት ነው።

፱. ሩት 4፥6 ላይ የራሴን ርስት እንዳላበላሽ ሲል ምን ማለቱ ነው?

መልስ፦ ሁለት ሚስት አግብቼ ማስተዳደር እንዳያቅተኝ ለማለት የተናገረው ነው። ርስቴ ሲበዛ እንዳይጠፋብኝ ማለቱ ነው። ርስት ሲበዛ ይጠፋልና።

፲. "እንግዲህ ታጠቢ፥ ተቀቢ፥ ልብስሽን ተላበሺ፥ ወደ አውድማውም ውረጂ፤ ነገር ግን መብሉንና መጠጡን እስኪጨርስ ድረስ ለሰውዮው አትታዩው" ይላል (ሩት 3፥3)። የዘመኑ የአለባበስና የቅባት አጠቃቀም ሁኔታ (አጠቃላይ ለማጌጥ የሚደረጉ ነገሮች) ከዚህ ጥቅስ አንፃር ተቀባይነት የለውም ወይ? ለማጌጥ መሆን ያለበትስ (የሚፈቀደው) እስከምን ድረስ ነው?

መልስ፦ አለባበስ፣ መታጠብ፣ ሽቱ መቀባትና ሌሎችም ኃጢአት የሚሆኑት ለዝሙትና ለትዕቢት የሚጋብዙ፣ ሌላውን የሚያሰናክሉ ሆነው ከተገኙ ነው። ከዚህ መሠረታዊ ሐሳብ ሳናፈነግጥ ብንታጠብ፣ ብንለብስ ምንም ችግር የለውም። የዘመኑ አለባበስም መለካት ያለበት በዚህ ሂደት ነው። ለፍትወት የሚዳርግ ከሆነ መተው ይገባል።

## የመጽሐፈ ሩት ማስታዎሻ

**ምዕራፍ 1፦** -መሳፍንት ይገዙ በነበረ ጊዜ በሀገሩ ላይ ረኀብ መሆኑ፣ አቤሜሌክም ከሚስቱና ከሁለት ልጆቹ ጋር ከይሁዳ ቤተልሔም ተነሥቶ ወደሞዓብ ምድር መሄዱ፣ የሚስቱ ስም ኑኃሚን እንደሆነ

-አቤሜሌክ በተሰደደበት ሀገር መሞቱ፣ ልጆቹ ከሞዓብ ሴቶችን አግብተው እንደኖሩና ትንሽ ቆይተው እንደሞቱ

-ኑኃሚን ከሁለት ምራቶቿ ጋር ብቻዋን መቅረቷ፣ በሞዓብ ምድር ሳለች እግዚአብሔር ሕዝቧን እንደጎበኘ መስማቷና ወደሀገሯ ለመመለስ መወሰኗ፣ ምራቶቿን ግን መርቃ ወደወገኖቻችሁ ተመለሱ ማለቷ፣ የአንዱ ልጇ ሚስት ዖርፋ ወደወገኖቿ መመለሷ

-ሩት ኑኃሚንን ወደምትሄጂበት እሄዳለሁ ሕዝብሽ ሕዝቤ አምላክሽም አምላኬ ይሆናል በምትሞችበትም እሞታለሁ ብላ ተከትላት መሄዷ

**ምዕራፍ 2፦** -ሩት ከቦዔዝ እርሻ አጫጆች ኋላ ኋላ እየሄደች በእርሻ ውስጥ መቃረሟ፣ ቦዔዝም ቃርሚያ ለመቃረም ወደሌላ እርሻ አትሂጂ ከዚሁ ቃርሚ እንዳላት፣ ለኑኃሚን ያደረገችላትን መልካም ነገር ሰምቶ እንደመረቃት፣ የተጠበሰ እሸት እንደሰጣት፣ የቃረመችውን ወቅታ ወደኑኃሚን እንደወሰደችው

**ምዕራፍ 3፦** -ኑኃሚን ሩትን ታጥበሽ፣ ተቀብተሽ ወደ ቦዔዝ አውድማ ውረጂ እንዳለቻት፣ ሩት አማቷ ያዘዘቻትን ሁሉ እንዳደረገች፣ ቦዔዝ ስድስት መሥፈሪያ ገብስ ሠፈሮ ለሩት እንደሰጣት

**ምዕራፍ 4፦** -ቦዔዝ ሩትን እንዳገባት፣ ሩትም ከእርሱ ወንድ ልጅን እንደወለደችና ስሙንም ኢዮቤድ እንዳለችው፣ ኢዮቤድ የዳዊትን አባት እሴይን እንደወለደ

## መጽሐፈ ሩት ላይ የጠየቅኋቸው ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

**፩. አቤሜሌክ ሚስቱን ኑኃሚንንና ልጆቹን ይዞ ወደ ሞዓብ የተሰደደ በምን ምክንያት ነበር?**

ሀ. በሀገሩ ጦርነት ስለነበረ　　ሐ. በሀገሩ በሽታ ስለሆነ

**ለ. በሀገሩ ረኀብ ስለሆነ**　　መ. ሁሉም

**፪. ኑኃሚን ወደሀገሯ ወደቤተልሔም ስትመለስ ሕዝብሽ ሕዝቤ አምላክሽ አምላኬ ይሆናል ብላ የተከተለቻት የልጇ ሚስት ማን ናት?**

**ሀ. ሩት**　　ሐ. ራኬብ

ለ. ዖርፋ　　መ. ራሔል

**፫. ሩትን አግብቶ ኢዮቤድን የወለደ ማን ነው?**

ሀ. አሚናዳብ　　ሐ. እሴይ

ለ. ቦዔዝ

መ. ነአሶን